# ሰደቅ አላማችን

በሰልስቱ ህብረ ቀለማት አሸብርቀሽ
ብሩህ ልምላመሽ
ርጉእ ሰላምሽ
ክቡር ሉአላዊነትሽ
ጣምራ የህዝቦችሽ አንድነት አርማ አቅፈሽ
ስትውለበለቢ ደረትሽ ነፍተሽ
ተቅበጠበጡ እርር ብለው ጋዩ
የህብረ ብሒር ሰንደቅ መሆንሽን ሲያዩ፤
ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ብለው በዙርያቸው
እንዳልከለሉሽ
ደርግ የሰው በላ አርማው እንዳልሸነቆረብሽ
ምነው አሁን በህብረ አንድነቱ አላዘንቡሽ፤
የዙፋናቸው መለያ............ስላልሆንሽ
ወይስ የአረመነነት አርማ ስላልሰቀልሽ፥
እንግዲህ ይብቃቸው በስምሽ ማላዘኑ
እነሱ የኖሩበት አክትምዋል ዘመኑ
ያገር የህዝብ መለያመሆንሽ እስኪያምኑ፤
ባንደራችን..........
የሰማየ ሰማያት ቅናት አርማሽ
ለእማዊት ሀገረ ክብር አጎናፅፈሽ
ምትሀታዊ ልዩ ሚስጥርሽ
በሰንደቁ ፅንአት ተክለሽ

አያት ቅድመ አያተ አንግበውሽ

እስከ ዘመንየ በክብር ያዘለቀሽ

በወር ተራየ ቃል ገባሁልሽ

ላይነግዱ በስምሽ

ለስልጣናቸው መለያ ላያረጉሽ

በስመ ባንደራ ላይከፋፍሉት ህዝቦችሽ

ከእንግዲህ ይወቁት............ምትሀትሽ

የብኅር ብኅረሰቦች የክብር ልባስ መሆንሽ።

ራሳቸው ከኢትዮጵያዊነት በላይ ኮፍሰው

ከጀሉ ሊነግሩን......ስለጥንቱ ባንዲራቸው

ባንዲራየ.............

ተካይሽ ለሀገሩ ሲቀላ

ስንደቁ አልተዋትም ኀዋላ

በደሙ ቀብትዋታል ደፋሩ አባ መላ።

ከእንግዲ ይብቃ በስምሽ ማላዘኑ

እነሱ የኖሩበት አክትምዋል ዘመኑ

ያገር የህዝብ መለያ መሆንሽን እስካመኑ

ባንደራየ

ቀድሞም ህዝባዊነት ነው ልብስሽ

የአገር አንድነት ልኡላዊነት ነው ሰንደቅሽ

የአብዝሀ ህብረ ብኅር አርማ መስቀልሽ

ፋና ወጊ ብሩህ ተስፋ ነው ብርሀንሽ፡

ለህዝባዊ አንድነት መለያሽ

ሁሉም ዘብ ይቆማል ለክብርሽ

ፍስሀ በላይ

ስቶክሆልም